የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በጎዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

መጋቢት ፲፱ እስከ መጋቢት ፳፭ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
March 28 to April 3, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፲፩
Volume I Number 11

## ድርጅቶችና የሕዝቡ ትግል

ያለ ጥያቄ፤ የሕዝብ ትግል ከግቡ የሚደርሰው፤ በድርጅት ሲመራ ነው። ይህ ድርጅት በትግሉ ሂደት የሚጫወተው ከፍተኛ ሚና አለው። የታጋዩን ኃይል ያሠባስባል። የትግሉን ግብና መንገድ በመንደፍ ለትግሉ አመራር ይሰጣል። ድርጅት ለሕዝቡ የትግሉ መሣሪያ ነው። ሕዝቡ ድርጅቱን በመጠቀም ታግሎ ከግቡ ይደርሳል። በዚች **እስከመቼ ቁጥር ፲፩** በትግላችን የድርጅቶችን ሚናና አስተዋፅዖ እንመረምራለን።

አንድን ድርጅት ቆሰለ፣ ደማ፣ ለፋ ብሎ መመፃደቅ ትርጉም የሚሠጠው ድርጅታቸውን እንደጣዖት ለሚያመልኩ ታጋዮች ብቻ ነው። የቆሰለው፣ የደማው፣ የለፋው፤ ድርጅቱን መጠቀሚያ አድርጎ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋዕትነት የከፈለው ወጣቱ ታጋይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ያለ ድርጅት ትግሉን የሚያልሙ የዋሆች ናቸው። በነዚህ ሁለት ፅንፎች መካከል እውነታው ቤት ይመታል። በአለፉት ጥቂት አስርታት ዓመታት፤ ብዙ ድርጅቶች በትግላችን ሂደት ተከስተዋል። ቅርፃቸውና ይዘታቸው፣ መልካቸውና አመራራቸው፣ ታሪካቸውና ጥንካሪያቸው፤ እንደቁጥራቸው የበዛና የተለያየ ነው። ነገር ግን የትግሉ ታሪካዊ ሂደት ይወስዳቸዋል ተብሎ የተገመተው የመሰባሰብ ጉዳይ ከሃቅነቱ ይልቅ ምኞቱ ተስፋ ሆኖ ባለንበት ዳክረናል።

**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!** የድርጅቶችን ታሪክ ስንመረምር፤ ከድርጅት መርሃ ግብርና ከርዕዩታቸው ይልቅ፤ መሪዎቻቸው ይታወቃሉ። በአብዛኛው በድርጅት ስማቸው ሣይሆን የእከሌ ድርጅት በመባል ይታወቃሉ። የሚያስገርመው፤ ይህ ኩኔት፤ በውጭ አባላት የተወሰነ ሳይሆን፤ በድርጅቱ አባላትም ዘንድ ያለ ሃቅ ነው። እናም ድርጅቶች የመሪዎቻቸው መጠቀሚያ በመሆን ያገለገሉና እያገለገሉ ናቸው። የድርጅቶች አባላትም፤ ድርጅቶችን መገልገያ አድርገው ለሕዝቡ ፍላጎት መጠቀሚያ ከማድረግ ይልቅ የየድርጅቶቻቸው አገልጋዮች ሆነዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንድ በድርጅቶች ውስጥ ማዕከላዊነት ማዕከላዊ ቦታውን ተንፈራቆ ተዘፍቆበታል። በተጨማሪም፤ ድርጅቶች ትግሉን የግል ንብረታቸው አድርገው የሚመለከቱበት መነፅር ብቻ ስላጠለቁ፤ እነሱ ሥልጣን ላይ ካልወጡ ትግሉ ግቡን አይመታም በሚል መንፈስ ነው የሚንቀሳቀሱት። ለዚህም ነው ትብብር ሊመሠረት ያልተቻለው። አንድ አውራ ብቻ መኖር አለበት እሱም እኔ ነኝ በሚሉ መካከል መተላለቅ እንጅ መተባበር ሊኖር አይችልምና።

**ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ!** ባለፈችው የ**እስከመቼ** ዕትም፤ በግለ ሰብ ደረጃ የያንዳንዳችንን ታሪካዊ ግዴታ ጠቁመናል። በዚች የ**እስከመቼ** ዕትም ደግሞ፤ ባሉበት ድርጅት ውስጥ የድርጅትዎን ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ቅደም ተከተል ይጠይቁ ዘንድ በቂ ጥቆማ ሰጥተንዎታል። ባሁኑ ሰዓት፤ በኤርትራ ምድር፤ በተለያዩ የብሔርና ሀገር አቀፍ ስሞች የተሰባሰቡትን ኃይሎች ባንድ ግንባር ሥር አቆላልፎ፤ ሀገር ቤት የሥልጣን ክፍተት ይፈጠራልና፤ ቦታውን ለመሙላት የሚያደባ ቡድን አለ። በአንፃሩ ደግሞ፤ ከገዢው ቡድን በመለጠፍና በመለማመጥ የሥልጣን ትራፊ የሚማጠኑ አሉ። በኛ አመለካከት ሁለቱም ክፍሎች መሠረታዊ በሆነው የትግሉ ባለቤት ላይ እምነት ይጎድላቸዋል። *ትክክለኛ የሕዝብ ድርጅት አባላት በሕዝቡ መካከል ተገኝተው፣ ሕዝቡን አንድ እርምጃ በመቅደም የሕዝቡን የዕለት ከዕለት የኑሮ ጥያቄ አብረው አንግበው እየታገሉ፣ አጠቃላይ ትግሉን ከዋነኛው የነፃነት ትግል አኳያ አመራር በመሥጠት፤ አንድ ትግል፣ አንድ ሀገር፣ አንድ ሕዝብ ብለው የሚነሱ ናቸው።*

**የእስከመቼ ዕትም የዝግጅት ቦርድ፤**
ድረስ ነጋ፣ ሕሊና ነጋሣና፣ ሀገሬ ተመቼ
eske.meche@yahoo.com